የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፱
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፭ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 29
ADDIS ABABA 24th March 2009

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፷፭/፪ሺ፩

የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……………ገፅ ፬ሺ፮፻፷፱

## CONTENTS

Regulation No. 165/2009

Ethiopian Postal Service Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation……………. Page 4669

### ደንብ ቁጥር ፩፻፷፭/፪ሺ፩

### የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩) (ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፭/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪. መቋቋም

፩. የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እና ወኪሎች በአዲስ አበባና እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ሥፍራዎች ሊኖሩት ይችላል።

### Regulation No. 165/ 2009

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN POSTAL SERVICE ENTERPRISE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

This Regulations may be cited as the "Ethiopian Postal Service Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 165/2009."

2. *Establishment*

1/ The Ethiopian Postal Service Enterprise (hereinafter referred to as "the Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices and agents in Addis Ababa and in any other place as may be necessary.

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

